ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party
(Kinijit)

***ዜና ነክ መግለጫ፤ News Release:***

**በኢትየጵያ የህሊና እስረኞች ላይ የታሰበውን የካቲት 12 1999ቱን የፍትህ ቧልቲ አስመልክቶ::**

***In relation to the coming Feb 19 2007 sham trial of prisoners of conscience in Ethiopia:***

**የከቲት 3 1999… ቁጥር 2**
February 10, 2007… NO **2**

## የሃገር ውጭ ዜና

### የሻማ በማብራት ሰልፍ በለንደን

- በየካቲት 9 1999 በትናንት እለት በእንግሊዝ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስቴር መኖሪያና መስሪያ ቤት ፊት የሻማ መብራት ትእይንት ህዝብ አድርገዋል:: በየካቲት 12 1999 አም ወያኔ በግፍና በእብሪት ባሰራቸው የቅንጅት መሪዎች፣ጋዜጠኞች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ላይ በፍትህ ስም ሊውስድ ያሰበውን የእብሪት ውሳኔ በመኮነን ይህ ውሳኔ ከመወሰዱ በፊት የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር የአንድ ሰሞን ባልደረባቸው የነበረውን መለስ ዜናዊን ተው እንዲሉት የሚጠይቅ ነበር:: ሰልፈኛው ይህ በእብሪትና በሃሰት የተሞላ የብይን ውሳኔ፣ መለስ ዜናዊ በግሉ በመረጣቸውና በሚያዛቸው ዳኞችና የራሱ ነጻነት በሌለው የፍትህ ስርአት አማካይነት ቢፈጸም በሃገሪቱ ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚገልጽና ጠቅላይ ሚኒስትሩም እንዲህ አይነቱን አደጋና የፍትህ መጨንገፍ የማስቆም የታላቅ መሪነት ሃላፊነትና የታሪክ ግዴታ እንዳለባቸው የሚገልጽ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው አድርጓል:: ቁጥሩ በመቶዎች የነበረው ሰልፈኛ የለንደን ብርድ እያንቀጠቀጠው ሻማ እያበራ ፊሽካና ጥሩባውን እያሰማ ጠቅላይ ሚኒሰትሩን የሚያሳስቡ የተለያዩ መፈክሮችን ለሰአታት አሰምቷል:: ከእነዚህ መፈክሮች መሃል «ቶኒ ብሌየር በኢትዮጵያ ነጻነት ተከሷል! ፍትህ እራሱ ተከሷል! ዴሞክራሲ ተከሷል! የመለስ ዳኞች ሲፈርዱበት ዝም ካልክ፣ ነጻነት ዴሞክራሲ ፍትህ በኢትዮጵያ ይሞታል:: በማየሻማ ቋንቋ ድምጽህን አጉልተህ ተናገር:: በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰብአዊ መብት እረገጣ አውግዝ:: ሌሎችም የአለም መሪዎች እንዲያወግዙ አድርግ» የሚሉ መፈክሮች ይገኙበታል:: ለናሙና ያህል የቀረጽነው ደምጽ የሚቀጥለውን ምልክት በመጫን ያድምጡ( ):: የሻማ ማብራቱ ሰልፍ ከሰአት በኋላ በ4 ሰአት ጀምሮ ከምሽቱ 2.00 ሰአት ሲሆን ተጠናቋል:: ሰልፈኛውም በሚቀጥለው ሳምንት ፌብሩዋሪ 16 በወያኔ/ኢህአዴግ ኤምባሲ ፊትለፊት ለመገናነትና በአለም አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው የኢትዮጵያውያን የተቃውሞ እለት አካል ለመሆን ቀጠሮ ሰጥቶ ተበትኗል
- **ኢንድፔንደንት ጋዜጣ መለስ ዜናዊን አጋለጣው::** በእዚህ እለት በእንግሊዝ ሃገር በየእለቱ በመታተም የሚወጣው ዘ ኢንዲፔንደት የተባለ ታዋቂ ጋዜጣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰብአዊ መብት በመጣስ፣ ፍትህን በመርገጥ፣ የሲቢል መብቶችን በማፈን የለየለት አምባገነን መሆኑን የሚገልጥ የሙሉ ገጽ ሃተታ ለአንባቢው አቅርቧል:: በሚቀጥለው የካቲት 12 1999 የመለስ መንግስት አለምአቀፍ ህብረተሰቡና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የህሊና እስረኞች ብለው የፈረጇቸውን የቅንጅት መሪዎች ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችንን ለብይን አረርባለሁ ብሎ ሽር ጉድ ማለቱ የእዚሁ የመለስ ዜናዊ የአምባገነንነት መገለጫ ነው ሲል ተችቶበታል:: ጋዜጣው

በተለይ ዝነኛውን አለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምነስቲ አለምአቀፍን በመጥቅስ «ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ከየቤታቸው እየተለቀሙ በውሸት ክስ እንደሚታሰሩ» ከገለጸ በኋላ «ከሁሉም በላይ አሳሳቢ የሆነው የመንግሰት የጸጥታ ሃይሎች ግለሰቦችን ከቤታቸው ጎትተው በማውጣት በደጃፋቸው ላይ በመግደል የሚፈጽሙት የነጻ እርምጃ እንደሆነ ዘግቧል።» የጋዜጣውን ሙሉ ቃል ለማንበብ የሚቀጥለውን መሸጋገሪያ ይጫኑ።( )

- ***ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ህዝብ የትግል ጥሪ አቀረበ።*** መጪውን የካቲት 12 አስመልክቶ በሃገር ውስጥ የሚገኘው ኢትዮጵየዊ በውጭ የሚገኙት ወገኖቹ ጋር በመሆን በጋራ ማድረግ ስለሚገባው የትግል እንቅስቃሴ ጥሪና መመሪያ የሚሆን ጋዜጣዊ መግለጫ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አወጣ። መግለጫው የኢትየጵያን ህዝብ የዘመናት የነጻነት ተጋድሎ ካደነቀና ህዘብ ለመብቱ ለነጻነቱና ለዴሞክራሲ የከፈለውን መስዋእትነት ካወሳ በኋላ ወያነ/ኢህአዴጌ የካቲት 12 1999 አም በሃሰት ክስ በሳራቸው የህሊናና የፖለቲካ እስረኞች ላይ ሊፈጽም ያሰበውን ወንጀል በመቃወም የሚቀጥሉትን የተቃውሞና የተማጽእኖ እርምጃዎች የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲወስድ ጥሪ አቅርቧል። «ለፍትህ ዘብ መቆም ታሪካዊ ግዴታ ነው» በሚል እርእስ የወጣው መግለጫ በኢትዮጵያ ህዝብ እንደእምነቱ በስፋት በየቤተክርስትያኑና በየመስጊዱ በመሰባሰብ ግፍ ባሀገራችን እንዲያበቃ የታሰሩት ንጹህን የፖለቲካና የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ እርቅና ሰላም በሃገራችን እንዲሰፍን ፈጣሪያቸውን እንዲማለዱ ጠይቋል። የሰላመዊ የትግል ስልት በጥንቃቄ በመጠቀም ተማሪው ትምህረት በማቆም ሽማቹ ቀድሞ የተደረገለትን ጥሪ በማጠናከር የወያኔንና ከወያኔ ጋር ቅርበት ያላቸውን የንግድ ተቋማት ምርቶች ባለመግዛት የሚሰጡትን ግላጋሎቶች ባለመጠቀም ተቃውሞውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርቧል። በተለይ የወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ዜጎች በንብረታቸውና በገዛ ሃብታቸው ላይ የማዘዝ ተፈጥሮአዊና የዜግነት መብት የገፈፈ በመሆኑ የህዝብ ተቃውሞ ንብረቱንና ህይወቱን በወያኔ ዘራፊዎችና ገዳዮች አደጋ ላይ ሳይጥል ተቃውሞውን መግለጽ የሚችልባቸውን አግባቦች አስቀምጧል። የመዝናኛ የሲኒማ የቲያትር ቤቶችን ከወያኔ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሆቴሎችን እንዲሁም የከተማውን አውራ ጎዳናዎች ጭር እንዲሉ በማድርግ ተቃውሞን መግለጽ ስሚቻልባቸው መንገዶች መግለጫው መመሪያ ሰጥቷል። የመግለጫውን ሙሉ ቃል ለማንበብ የሚከተለውን ይጫኑ። ( )

## ***<u>የዲፕሎማሲና የሎቢ ዜናዎች</u>***

- **የአሜሪካን መንግስት አምባሳደር** በኢትዮጵያ አቶ ያማሞቶ የቅንጅትን መሪዎች ጋዜጠኞችንና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን በእስር መንገላታትና የሃስት ክስና የሃሰት የብይን ደባ በሚመለከት በአሜሪካ ከሚገኙ የቅንጅት ደጋፊዎች ለተጻፈላቸው ደብደቤ በሰጡት ምላሽ መንግስታቸውም ሆነ የአለምአቀፍ ማህበረሰቡ ይህ ጉዳይ የሚያሳስበው እንደሆነና ጉዳዩ እስረኞቹን በመፍታት እንዲጠናቀቅ ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። በአሜሪካ መንግሰት በኩል እንዲህ አይነቱ ፍላጎት እንዳለ ቢታወቅም አምባሳደሩ መንግስታቸው በመስራት ላይ ነው ስላሉት ጉዳይ የሰጡት ማብራሪያ የለም። እንዴትስ የሃገሩን ህዘብ እያሸበረ በሌላ ሃገር ሽብርተኛነትን እዋጋችኋለሁ ለሚላቸው አስመሰይ የሚሰጡት ወታደራዊ ዲፕሎማሲዊና የገንዘብ ድጋፍ መንግስታቸው ያሳስበኛል ከሚለው የህሊና አስረኞች ጉዳይ ጋር አብሮ እንሚሄድ ደብዳቤያቸው የሰጠው ፍንጭ የለም።
- **ጋናዊ የኢትዮጵያ ወዳጅ** በሌላ በኩል ለመጀመሪያ ግዜ በአፍሪቃ ውስጥ በሃገራችን ውስጥ የሚካሄደው የሰብኣዊ መብት ረገጣ፣ የህሊናና የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ የሚያሳስባቸው፣ ለእዚህም ሃላፊነት በመውሰድ በአፍሪካ የፖለቲካ ተቋማትና የፖለቲካ መድረኮች ጉዳዩን ለማንሳት ቆርጠው የተነሱ አፍሪቃዊ አጋር የኢትዮጵያ ህዝብ አግኝቷል። በጋና ፓርላማ ውስጥና በፓን አፍሪካ ፓርላማ ውስጥ መቀመጫ ያላቸው ተመራጭ የተከበሩ አቶ መሃማ የኢትዮጵያን ፖለቲካና የሰብአዊ መብት ረገጣ የአፍሪቃ ህብረት መሪ ሆነው ለተመረጡት የጋናው ፕሬዚደንት እንዲሁም ለኮመን ዌልዝ ሃገሮች የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ተቋም እንዲሁም ለፓን አፍሪካ ፓርላማ እንደሚገልጹ

አስታውቀዋል:: በጋና ውስጥም ለመገናኛ ብዙሃኑ ስለኢትዮጵያ መግለጫ መስጠታቸውንና በሃገራቸው ስላም እርቅ ዴሞክራሲና ፍትህ እንዲሰፍን ከሚፈልጉ ኢዮጵያውያን ጋር በቅርበት ለመስራት ፈቃደኛነታቸውን ገልጸዋል:: «የኢትዮጵያ የህሊና እስረኞች ጉዳይ የአፍሪቃ የህሊና ቁስል መሆን አንደሚገባው» አመልክተዋል::

## ***<u>የሃገር ውስጥ የፍትህና የሰብአዊ መብት ዜና</u>***

- **ወያኔ ኢህአዴግ ከህግ ውጭ በስፋት ማሰሩን ቀጥሎበታል**:: በተያዩ በታዎችም የደርግን ግፍ ዘመን የሚያስታውስ ነጻ እረምጃ በግለሰቦች ላይ በመውሰድ ግድያ ፈጽሞ አስከሬንን ጎዳና ላይ ጥሎ መሄድ ጀምሯል:: በመላው ሃገሪቱ በየክልሉ እስር ቤት የሚታጎረው እስረኛ ቁጥሩ አየናረ በመሄድ ላይ ይገኛል:: ከየክልሉ አዲስ አበባ ድረስ የተላኩት አስረኞች ቁጥር ባለፈው ወር ብቻ በመቶዎች ጨምሯል:: ወያኔ/ከጥቂት ወራት በፊት በቅንጅት አባትና ደጋፊዎች ላይ በተያዩ ሰበቦች የሚወስዳቸው እርምጃዎች አንዳንድ በነፍሳቸው የቆረጡ የራሱ ዳኞችና ባለም አቀፍ ህብረተሰቡም ፊት እያሳጣ በመምጣቱ ሰሞኑን የሚያስራቸውን እስረኞች ክስ ጠመንጃ ካነሱ ድርጅተች ጋር በማቆራኘት የቅንጅትን ደጋፊዎች በአርበኞች ግንባር አባልነት የመክሰስ አዲስ የሃሰት ክስ ማቅረብ ጀምሯል:: ከጥቂት ወራት ጀምሮ በወያኔ የታሰሩ የቅንጅት ደጋፊዎች ክስ ጠመንጃ ካነሱ ሌሎች ድርጅቶች ጋር ተቆራኝቶ አንዲቀርብ ለፖሊስና ለአቃቤ ህጉ መመሪያ የተሰጠው ከጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ በራሱ በለስ ዜናዊ ትእዛዝ እንደሆነ የእስረኞች ጉዳይ ለፍርድ ቤት አንዲያዘጋጁ ሃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሰት ተቀጣሪ ለቅንጅትና ለአነድነት ፓርቲ በላኩት መልአክት ተረጋግጧል::